

Amhara Association in The Netherlands

PRESS RELEASE
ጋዜጣዊ መግለጫ
JANUARY 2026

# ለአማራ የጦርነት ተጎጂዎች የሚውል የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በጥር ወር ተጀምሯል

በአማራ ህዝብ ላይ እየተደረገ ያለው ስልታዊ የዘር ጭፍጨፋ ከተጀመረ ከሶስት አስርት አመታት በላይ መቆጥሩ ይታወቃል። አሁን ባለንበት አምስት አመታት ውስጥ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ጦርነት ታውጆበት በመቶ ሺዎች ለሞት ፥ በሚሊዮኖች ከቀያቸው ለማፈናቀል እና ለሰው ሰራሽ ረሀብ እንዲሁም ከ አምስት ሚሊዮን በላይ ህጻናት እና ወጣቶችን ደግሞ ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይገኙ አድርጓል።




ይህንን ስቃይ እና ሰቆቃ መመከት እንዲቻል ፤ የአማራ ወጣቶች ተደራጅተው ጦርነቱን በአስደናቂ ሁኔታ እየመከቱ ቢሆንም በተለያዩ አካባቢዎች ጦርነትን ሸሽቶ የተፈናቀለ እና በረሃብ አለንጋ የሚገረፍ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ መኖሩ ይታወቃል።

ለነዚህም ተጎጂዎች መሰረታዊ የምግብ ፥ የንጽህና መጠበቂያ ፥ የመድሃኒት እና የአልባሳት እረዳታ ማድረግ እንዲቻል ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀደም በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደተደረገው የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ ይህንን የገቢ ማሰባሰቢያ መንገድ አዘጋጅቷል።

ይህንን ክፉ ግዜ ለመሻገር ፥ ወገኖቻችንን ለመርዳት እና የታሪክ እና የህሊና ተወቃሽ ላለመሆን ከአንዲት ዩሮ ጀምሮ አቅማችሁ እስከቻለው ድረስ በአማራ ማህበር በኔዘርላንድ የባንክ አካውንት ማለትም “**Vereniging van Amharas in Nederland**” “**NL07 INGB 0108 1617 81**” በሚያስገቡበትም ግዜ የመላኪያ ምክንያት ላይ “**INK_NOODFONDS**” የሚለውን መለያ (betalingskenmerk / reference) በመጨመር ቢልኩ ማህበሩም የተቀበልነውን አደራ ለተጎጂዎች ወገኖቻችን በማድረስ የቆመበትን አላማ እና ግዴታዎቹን እንደሚወጣ ገልጿል።




**Amhara Association in The Netherlands**

**PRESS RELEASE**
ጋዜጣዊ መግለጫ
**JANUARY 2026**

# በዚህም ወር የቀጠለው የአማራ ህዝብ ሰቆቃ እና ተያያዥ ጉዳዮች

“ባሳለፍነው ጥር ወር ልክ እንደከዚህ ቀደሞቹ በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ሁሉ በተለያዩ የጦርነት ቀጠናዎች እንዲሁም የንጹሃን ዜጎች የመኖሪያ እና መገበያያ ስፍራዎች ላይ ሲደረግ ቆይቷል። ከነዚህም በጥቂቱ ራያ ቆቦ ፥ ቡግና ፥ ባህር ዳር ዙሪያ ፥ ጠለምት ፥ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ አንዳንድ ወረዳዎች ፥ ሰሜን ጎጃም እና ሰሜን ጎንደር ፥ ላሊበላ ፥ ምስራቅ ወለጋ ፥ ደምበጫ ፥ ቋሪት ፥ ጉና በጌምድር ፥ ዋግ ህምራ እና መተከል ይገኙበታል።”



“በብዙ የዜና አውታሮች እንደተዘገበው እና አማኔ ም ማጣራት አድርጎ እንዳረጋገጠው በ**ጥር 15, 2026** በዋግ ህምራ ከመጫሃ ወረዳ ወጣ ብላ ሰፋ ድልድይ አቅራቢያ በምትገኝ ቦታ ላይ የአገዛዙ ድሮኖች በፈጸሙት ጥቃት ከ **40** በላይ የሚሆኑ የራሱን የአገዛዝ የሚሊሻ ተዋጊዎች ሲሞቱ ከ **16** በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶቻቸው አቅራቢያቸው ወደሚገኝ የጤና ተቋም መወሰዳቸው ተገልጿል።”

“በአማራ ክልል እየተደረገ ባለው ጦርነት በአገዛዙ የሚፈጸሙ የጾታዊ ጥቃትን እንደ ጦር መሳሪያ የመጠቀም እስትራቴጂ አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን እና ተጎጂዎችም ከጥቂት ወራት በፊት በ ቢቢሲ ከተዘገበው ቁጥር ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየታቸውን ተረድተናል። ይህም ከፍተኛ የማህበረሰብ ቀውስ እያስከተለ እና የጥቃቱ ሰለባዎችም ለአምሮ ህመም ሲቀጥልም ወደ እራስ ማጥፋትም እየሄዱ እንደሆነ ዘገባዎች ገልጸዋል።”

“በሰላም እጦት እና በኑሮ ውድነት እየተገረፈ ያለው የአማራ ህዝብ እና መላው ኢትዮጵያዊ ከነዚህ ተግዳሮቶች ለመውጣት እያለመ ባለበት ሁኔታ አገዛዙ ዘጠናኛ አመት የአየር ሃይል መስረታ በአል አከብራለው በሚል ከተለያዩ የውጭ ሃገራት ተበድሮ እና ገዝቶ ያመጣቸውን ዘር ጭፍጨፊ ድሮኖች ፥ ጀቶች ፥ የጦር አውሮፕላኖች ፥ ሂሊኮፍተሮች እና ሌሎችንም በሰማይ ላይ ትርኢት ሲያደርግ የታየበት ወር ሆኖ አልፏል። ይህም ሃገር ውስጥ ካሉ ሃይሎች እየተደረጉ ያሉ  እና ከጎረቤት ሃገራት ጋር ሊደረጉ የታሰቡ ጦርነቶች አይቀሬ መሆናቸውን እና አገዛዙ ከጦርነት ውጪ ምንም ሌላ አማራጭ  እና መፍትሄ እንደማያስብ አሳይቷል።”




Amhara Association in The Netherlands

PRESS RELEASE
ጋዜጣዊ መግለጫ
JANUARY 2026

# የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ የአፋብን ምስረታ አስመልክቶ በጥር 23, 2026 የሰጠውን መግለጫ በተመለከተ

አማኔ በጻፈው የድጋፍ እና የደስታ መግለጫ እንዳመላከተው ፥
የአማራን ህዝብ በጠላትነት እና በአጥቂነት የሚፈርጅ እና በጥላቻ-ተኮር የሃሰት ትርክቶች ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካዊ ስርዓት መምጣቱን ተከትሎ መላው የአማራ ህዝብ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ለሁለንተናዊ ስርዓት-መር ጥቃቶች እና ጭቆናዎች መጋለጡ በአደባባይ የተገለጠ እውነት ነው። ይህም መንግስት-መር ጥቃት ከእለት ተለት አስተዳደራዊ መድሎ እስከ ህልውና ስጋት ድረስ የተዘረጋ መሆኑ ይታወቃል።

ይህንንም በመረዳት እና የተደቀነውንም የህልውና ስጋት ለመቀልበስ ያለሙ ተናጠላዊ እና ቡድናዊ ትግሎች በአማራ የቁርጥ ቀን ልጆች ሲደርጉ ቆይተዋል። ሆኖም ግን ጥቃቱ እና የህልውና ስጋቱ እየተባባሰ ከመሄዱ ባሻገር በፖለቲካዊ አደረጃጀቶች እና ቀድመው በነቁ የአማራ ልጆች ሲደረጉ የቆዩት የትግል ስልቶች የተፈለገውን ሁሉን አቀፍ ድል ማስመዘገብ አልቻሉም ነበር።

ስለሆነም ከ**ጥር 5 ፥ 2018 ዓ.ም** ጀመሮ የአማራ ህዝብ ትግል በአንድነት እና በወጥነት የሚመራበት ተቋማዊ አሰራር እና ትግሉን የሚመራ ድርጅት በይፋ ተበስሯል። ይህንንም ተከትሎ የአማራ ፋኖ ብሄራዊ ንቅናቄ (አፋብን) በአማራ ህዝብ ላይ የተደቀነውን የህልውና ስጋት ለመቀልበስ እና ስር ነቀል የስርዓት ለውጥ በማምጣት የእኩል እድል ተጠቃሚነት፣ ፍትህ፣ ነጻነት እና የህግ የበላይነት የተረጋገጡባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን የማድረጉን ትግል የሚመራ ድርጅት ሆኖ ተወልዷል።

ለዚህም አኩሪ ድል የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ አባላት ታላቅ ደስታ ተሰምቷቸዋል። የአንድነት መድረኩ ሁሉንም አማራ በእኩልነት እና በአንድነት ያቀፈ ሆኖ እንዲቀጥል ሁሉም የድርሻውን ገንቢ ሚና እንዲጫዎት ጥሪ በማስተላለፍ ፥ አዲሱ የትግል አንድነት ከግለሰቦች ሽኩቻ የጸዳ ፥ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እና ከግል እና የቡድን ፍላጎቶች ይልቅ የተከበረውን የአማራ ህዝብ ያማከለ እንዲሆን በማሳሰብ ውህደቱን በሙሉ ልባቸው የሚደግፉት መሆኑን በታላቅ አክብሮት ገልጸዋል።

ሙሉ መግለጫውን በማህበሩ ድህረ ገጽ እና በማህበራዊ ሚዲያ አማራጮቻችን ገብተው ማንበብ ይችላሉ።